# ፍርሃትና ቤተዘመዶቿ

ዳኛቸው ቢያድግልኝ

ስለፍርሃት መሰረተሃሳብ  ጥሩ የሆነ ውይይት በኢሳት የምንአለሽ መቲ ፕሮግራም የቀረበውን ተመለከትኩ ጥሩ የውይይት ጅምር ነበር። የትናንቱን ድፍረት ከዛሬው ፍርሃት ጋር ለማጣቀስ የተሞከረውንም አየሁና በአንድ ወቅት እንደቀልድ የጀመርኩትን ጽሁፍ ከዚህ ጉዳይ ጋር እንዲጣጣም አድርጌ እንዳጋራው ተደፋፈርኩ። ከተለያየ ዘርፍ የመጡ ወገኖች በጉዳዩ ላይ እውቀት አጋርተው የሀገራችንን ሁኔታ ከፖለቲካው፣ ከማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች እንዲሁም ስነልቦናው ላይ ጫና የሚፈጥሩትን ያለፈባቸውን ሥርዐቶች እንዲሁም ባህልና ሃይማኖትንም አዳምሮ የሚይዝ ውይይት ቢኖር የቀረበውን ያጎለብተዋል የሚል እምነቴን ተናግሬ የበኩሌን ፍርሃትና ቤተዘመዶቿን እንዲህ ላስተዋውቅ።

ፍርሃት ከእናቷ ከልክየለሽ ጥንቃቄና ከአባቷ ነገን በምን አውቄ ትወለዳለች። ጀብድ ደግሞ ከአባቱ ካልደፈረስ አይጠራምና ከእናቱ ባወጣ ያውጣው ይወለዳል። ፍርሃትና ጀብድ ከተጋቡ አምባገነንን ይወልዳሉ። ፍርሃት ግን ግራ ቀኙን ለማየት ፋታ አግኝታ የታወቁት የወይዘሮ ማስተዋልና መምህር በእውቀቱን ልጅ ብልሁን ካገባች እነ ጥንቁቁንና አርቆ አሳቢን ትወልዳለች። በዚህ አይነት ቤተሰብ የተከበበች ፍርሃትም በመዋል በማደር ደንበር ደንበር ማለቷን የመተው እድሏ ሰፊ ነው።

የጀብድና የፍርሃት ልጆች የሆኑት አምባገነኖች ማንንም የማያምኑ አለቅጥ ፈሪዎችና ችኩሎች በመሆናቸው በገዳይነት ይታወቃሉ። እስኪደላደሉ ይቆዩና ስለነሱ የሚያውቁትን ሁሉ ያጠፋሉ። በተለይ ዘመናዊ ትምህርትን ከመሰሪ ኮሌጅ በአስመሳይነት ሰልጥነው ከተመረቁ ባህሪያቸውን መሸፋፈን ይችላሉና ብዙ ጉዳት ያስከትላሉሉ። ብልጣ ብልጥ ቃላት በመጠቀማቸው ብልህ ድንፋታና ዝርጠጣቸውን ደግሞ በጀግንነት አያሽሞነሞኑ የሚያወሩላቸው ከምላስ ብቻ የተሰሩ የሚመስሉ ካድሬዎችን በስፋት ያሰማራሉ።  ያለ ተቀናቃኝ ለረዥም አመታት ለመግዛት ስለሚሹ ጭንቅላታቸው እንደ ጋን ክፍት የሆነውንና ለከርስ ብቻ የሚያድሩ ሆድ አደሮችን ይሰበስባሉ። ለምሳሌ ከአህያ ጋር ለበርካታ አመታት ቅርበት የነበራቸው ሰው “በኔና በድርጅቴ ካመነ አህያም ቢሆን ሚኒስትር ይሆናል” ብለው ብዙ አህዮች መካከል ሆነው የስድብ ንፋስ ዘረጥ ዘረጥ ያረጉ የነበሩት አይነተኛ ምሳሌ ናቸው።  ትንሽ እንኳን የተቃወማቸውን በመዶሻ አናቱን በማጭድ እግር እግሩን ብለው ከጨፈላለቁ በኋላ ”ያለርስዎ እኛ ተስፋ የለንም” አስብለው ተስፋም እሳቸውም ተያይዘው ነጎዱ የሚባሉ ሰውም በትውስታችን ውስጥ አሉ።

ታድያ ጅብድ በደፈናው አይጠላም ምክንያቱም ጀብደኛ በብልህ ሲመራ በፍጥነት ለውጤት ያደርሳል። ጀብደኛ በራሱ መሪ ሲሆን ግን ለትውልድ የሚተርፍ ሰቆቃን ይወልዳል። መሳሳቱን ስለማይቀበል እስከመቼውም አይማርም። ችግሩ ጥፋት የማየት አቅሙም የተገደበ ነው። በመውደቅም ሆነ በመነሳት እርሱ ብቻ ገዝፎ ይታየዋል፣ ወዲያም ይቁም ወዲህ ድርጊቱ አውዳሚ ነው። በጊዜ ብዛት መማር ካልቻለ ለውድቀቱ ምክንያት የሆኑትን በመዘርዘር ወይ አድብቶ ቀን ይጠብቃል ወይም በየስፍራው እያማረረ ክስ ሲደረድር ይታያል። በመጨረሻ ደግሞ ውሎውንም ከቢጤዎቹ ጋር ብቻ ማድረግን  ስለሚመርጥ በትዝታ መኖርን እንጂ እውነታን የመመልከት አቅም ያንሰዋል። ወደ ህሊናው ለመመለስ የታደለ ከሆነ ግን ወይ ብልህና አስተማሪ ይሆናል ወይም የለየለት ፈሪ ይሆንና የምድሩን ነገር ትቶ የሰማዩ ላይ ያተኩራል። ጥቂት ለማመዛዘን የታደሉና  እውቀት የገራቸው ደግሞ ጀግናም ይሆናሉ። ስለትናንት ስህተት ሲመሰክሩ ስለ ፀፀታቸው ሲናገሩ ልብ ይሰርቃሉ። እንዲህ አይነት ምሳሌዎች ዙርያ ገባውን ሞልተዋል። ወደ ሕሊናው ያልተመለሰን ጀብደኛ የሚገላግለው ሞቱ ብቻ ነው።

የእውቀቱና የማስተዋል ሁነኛ ወዳጃቸው ፍላጎት ናት። ፍላጎት የጥበብ አንቀሳቃሽ ሞተሩ ናት። እንዲያውም አንዳንድ ፈላስፋዎች ፍላጎትና ንቃተሕሊና በመጋባታቸው የተወለዱት ናቸው በሁለት እግር ብቻ መሄድንና በቋንቋ መፈላሰፍን የጀመሩት ሲሉ ሁሉ ይደመጣል። ፍላጎት  ለብዙ ግኝቶች አንደርዳሪ በመሆን ትታወቃለች። ነገር ግን ለፍላጎት አለልክ ቦታ ከተሰጠ ወደ መንገብገብና መስገብገብ ስለምትሽጋገር እኔ ብቻ ለኔ ብቻ እያስባለች ወደ ጥፋት ልትመራ ትችላለች። ከትናንሽ ጸቦች አንስቶ እስከ አለምአቀፍ ጦርነቶችም ያደረሰቺው ይቺው በቅጡ ያልተያዘች ፍላጎት የተነኮሰችው ጠብ መሆኑን ታሪክ ፀሃፊዎች ያወሳሉ። ፍላጎት ከእውቀትና ማስተዋል ጋር እጅለእጅ ተያይዘው ከሰሩ ግን አግባብ ያለው ድፍረትና ጥንቃቄ የተሞላው ሙከራ እንዲያደርጉ ይገፋፋቸዋል። እንዲህ ያለውን ነገር ‘ሳይንሳዊ’ ይሉታል። ብልሁ በዚህ ባህሪው ነው የሚመሰገነው።

ፍላጎት ማብቂያ የሌላት በመሆኗ እውቀትና ማስተዋልን ስታበረታታ ትኖራለች። ለዚህ ነው  ሰዎች የጎሸን ዘር ወደምትታለብ ላምና ወደ’ሚያርስ በሬነት ያለመዱት፤ በዚህ በፍላጎት አነሳሽነት ነው የተኩላና የቀበሮ ዘር ውሻን ወደ ጥበቃ ሰራተኛነትና አዳኝነት፣ ዝሆንን ያህል ግዙፍ እንስሳ ደግሞ ወደ ጭነት አመላላሽነት የገሩት ለማለት ይቻላል። ዛሬ ከዚያም አልፈው የውሃ ቀዛፊን፣ የምድር ተሽከርካሪና የሰማይ በራሪን ፈጥረው በሌላ ፍላጎት ለሌላ እርካታ ሲንደረደሩ የምናየውም ለዚህ ነው። ፍላጎት ከእርካታ ጋር ፍቅር ቢኖራትም ሴሰኛ ናት ይላሉ እንዲያውም እነ ምንይሻላል፣ አልፎ አይቼውና አዲሱ  በርሷ ይታማሉ። ደግ የሚመኙ ሁሉ ግን ፍላጎት ወዲያ ወዲህ ከምትል ብልሁን አግብታ ብትኖር አለሟን እናይ ነበር ይላሉ። እንዲያውም ‘ሁለት ጊዜ ለካ አንድ ጊዜ ቅደድ’ የሚባለው ተረትና ምሳሌ ለፍላጎትና ብልህነት ነው ይባላል።

እነ ስልጣኔ የሙከራና የፍርሃት አጎራባቾች የነድፍረት ፍሬዎች ናቸው። ፍሬ ሁሉ ጣፋጭ እንዳልሆነ ሁሉ የስልጣኔ ውጤቶችም መራር የሚሆኑበት ጊዜ በርካታ ነው። ፍርሃት ግን ሺህ ፍላጎት ቢኖራት ምንም ማድረግ ስለማትችል መፍትሄ አልባ ትሆናለች። የፍርሃት ጀንበር ወይ አትጠልቅም ወይ አትነጋም ባለችበት እንዳለች መኖር ትሻለች። የሁሉም ወጀብ ግን ወዳሻቸው ይወስዷታል። እናም የባሰ አታምጣ ከማለት በቀር ምርጫ የላትም። ጀብድ ደግሞ ፍላጎቱን ለማሟላት ሲሻ አኪያሄዱ የአጥፍቶ መጥፋት አይነት ነው። የሁለቱ ፍሬ 'አምባገነንነት' የስልጣኔ ውጤትንም ለጥፋት የሚያውለው በዚህ የዘር ትስስሩ ነው። ታድያ ፍርሃትንም ሆነ ጀብድን በጥላቻ መመልከት ስህተት ነው። ብርሃን ብሎ ጭለማ እንዳለ ሁሉ መድፈር ብሎ መፍራትም ያለና የሚኖር ነገር ነውና። ቁምነገሩ ለጥሩና ዘላቂ ውጤት ለመድረስ እነዚህን ባህርያት መግራቱ ላይ ነው።

አንዳንዴ ሰዎች የሚፈልጉትን ቁልጭ ብሎ ማየት ካልቻሉ ባዩት ብቻ ይፈርጃሉ። የማሽላ ፍሬ የምታክል ትንሽ ዘር ዝግባን ወይም ባህርዛፍን የሚያክል ግዝፈት ያለው ዛፍ እንደሚወጣት ለተገነዘበ ግን እምቅ አቅሞችን በዋዛ አይመለከትም። አንዳንዶች የድሮ ኢትዮጵያዊ ጀግና ያሁኑ ፈሪ የሚል ድምዳሜም ለመስጠት ሲንደረደሩ ስናይ አስፈሪ የሚሆነውም ለዚህ ነው። ፍርሃት በደም የሚወረስ በተሞክሮና ትምህርትም የሚለመድ የእንስሳ ሁሉ ባህሪይ ነው። ኢትዮጵያዊን በደሙ ጀግና የምንልበት በቂ የታሪክ መረጃ አለ በተሞክሮው አይበገሬ የምንልበትም እንዲሁ። የቀን ጎዶሎ ፈርተው የሚያስፈሩ መሪዎችን ከሰጠው እነርሱም ወደዋናው ጠላት ሳይሆን ላለመበላት እርስበርስ ከተተራመሱ ያንን እምቅ ሀይል አብቦ ማየት ይልቁንም ያልከሸፈና ግብታዊ አብዮት የደም ጎርፍ የማይዘራበትን ለውጥ ማምጣት የማይቻል ይሆናል። ያኔ የፈሪ ስም ቢለጠፍም ክፉውን ቀን ጎንበስ ብሎ ማሳለፍ አማራጭ ይሆናል።

ጀብድንና ጀግንነትን ነጣጥሎ መመልከት ለዚህ መድሃኒቱ ነው። ሀገርን ያህል ትልቅ ወገንን ያህል ውድን ነገር በጀብድ በሽለላና ቀረርቶ ተነስቶ ባወጣ ያውጣው ብሎ ማጥፋት የሚከብደው ለዚህ ነው። የተለያየ ተሞክሮ፣ ትውስታና ታሪክ ያለውን ሕዝብ ደግሞ እርጋታውና ጥንቃቄውን ከፍርሃትና ደካማነት በመቁጠር መልሶ መላልሶ ማጣጣል ደግ አይደለም። ምክንያቱም ጉዳዩ የርስበርስ ነውና ጥፋቱ የከፋ ስለሚሆን ማለት ነው። ክብሪቷ አንዴ ከተጫረች ማጣፊያውም ያጥራል። ለይቶለት ወዲያና ወዲህ ሲቆም ደግሞ የትናንቱ የጦርነት ታሪክና የሕዝባችን ጀግንነት አንድ ትውልድ አንኳን አልተሸጋገረምና የዛሬው ትውልድ ፈሪ አይደለም!

ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ሊደርስባቸው ከሚችለው አደጋም በላይ ሊያደርሱ የሚችሉት ጥፋት እጅግ ሊያስፈራቸው ይችላል። በትግራይ ወሮበሎች ምክንያት በትግሬዎች ላይ የሚኖረውን የጥላቻ ክምር በዚህም ምክንያት በተጫረች እሳት ምን ሊከተል እንደሚችል ማሰብ እንኳን ያስፈራል። ስም መጥራት እንኳን እጅግ ስለሚያስፈራ የአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች... ከአንድ አካባቢ የመጡ ሰዎች የሚባለው ሃላፊነትን አጥብቆ ከመፍራትና ወደ አንድ ጥግ ላለመግፋት ነው። እነማን ናቸው ሲባል መልሱ አጭርና ቀላል ሆኖ ሳለ ማለት ነው። ከንብረት ዘረፋና ከስልጣን ሽሚያ በላይ ሰዎች በዘራቸው ሲዋረዱ፣ የጀግንነት ታሪካቸው ሲንቋሸሽና ሃይማኖታቸው ሲደፈር ሊያስከትሉ የሚችሉት ጥፋት ትንሽ ትልቅ ጥሩና መጥፎ የመምረጫ ጊዜ አይኖረውም እንደ ሰደድ እሳት እንደ እሳተገሞራም ነው።

አንዳንዶች ለውጥ የሚፈሩበት አመጻን የሚፈሩበት አንዱ ምክንያት ነገን አለማወቅ ነው። የወያኔ ሹማምንትና ቤተሰብ ለሊቱን ከሀገር ወጥተው ንጋቱ ላይ አራት ኪሎ ወና ቢሆን እንኳ ሊሆን የሚችለው የሚያስፈራቸው ሰዎች ከከሸፉ አብዮቶች መማራቸው ሊሆን ይችላል። የተበተነው ሲሰባሰብ... የተለያየው ሲገናኝ እያየን ነውና ሁኔታዎች በዚህ አይቀጥሉም ያኔ አምባገነኖችና ጎጠኞች ወዮላቸው።

ራስን ማወቅ አቅምን ማወቅ ለፍርሃት ፍቱን መድሃኒት ነው ይባላል። በፍርሃት ቆፈን ጠፍንገው የሚያስሩ አምባገነኖች ዋናው ዘዴያቸው ሕዝቡን ከነሱ የባሰ ፈሪ ማድረግ ነው። ዘግናኝ በሆኑ ቅጣቶች ሰቅጣጭ በሆኑ ግድያዎች ሽባ በሚያደርጉ ስለላዎች ወጥረው ይይዛሉ። ሰዎች አደጋውን ለመመከት ተነጣጥለው ስለሚንቀሳቀሱ በኔ እስካልመጣ ድረስ የሚል ማህበራዊ ስነልቦና እንዲኖር ይሆናል። ነገር ግን ሰዎች አቅማቸውን ካወቁና በጋራ ከቆሙ እንደሁልጊዜውም የጎሽ መንጋ መሃል እንደገባ አንበሳ ዘጠኝ ሞት አፍጥጦ መምጣቱን ያያሉ። ሰው ሲያስሩ ሁላችንንም እሰሩን፣ እዚህ ሰፈር ቤት እናፈርሳለን ሲሉ የዚያ ሰፈር ሰዎችም የኛንም ጨምራችሁ አፍርሱ ወይም አካፋና ዶማ ይዞ ወጥቶ የናንተንም እናፈርሳለን ቢላቸው ግራ ተጋብተው ወደ ልመናና ልምምጥ ይሄዳሉ። ብዙ ጊዜ የሆነው እንደዚያ ነው። ያጋቡብንን ፍርሃት ወደነሱ ስንመልሰው እንደ ውሻ ጭራቸውን ቆልፈው ዞር ይላሉ። አውርቶ አደሮቹ ሁሌም ከአሸናፊ ተቀላቅለው መኖርን ስለሚሹ የመንገድ ለውጥ ያመጣሉ። ለሆዳቸው ብለው የተቀላቀሉቱም የመጀመርያዎቹ ፈርጣጮችና ጠመንጃ አዟሪዎች ናቸው።

በዚህ ሁሉ ጎታች ሁኔታ ውስጥ ጠንክረው እየወጡ ያሉ ሀገራዊ ራዕያቸው ነጥሮ የወጣ ድርጅቶችን የመደገፍና የመቀላቀል እርምጃ እየታየ መሆኑ ሊያበረታታን ይገባል። ያሉት መንገዶች እየጠበቡ ተበታትኖ ከመሄድ በግድም ቢሆን አንድ መንገድ ላይ መገናኘት እየመጣ ነውና ተሳስቦና ተዛዝኖ ካሰቡበት ለመድረስ አስገዳጅ ሁኔታ ተፈጥሯል። በፍርሃት ምክንያት የሞተ ኑሮ ከምንኖር እስክንሞት በነፃነት መኖር ይሻላል። ስለዚህ ፍርሃታችንንና ጥርጣሬያችንን በእውቀት በእምነትና በማስተዋል እየገራን በአነስተኛ መስዋዕትነት የፍላጎታችንን እናገኝ ዘንድ ከጅምላ ፍረጃ ወደተሻለ የቅራኔ አፈታት እንሸጋገር። አዎ በፍርሃት ምክንያት የብዙ አመታት ሙትቻ ኑሮ ከመኖርና ይህንኑ በደምና ተሞክሮ ለትውልድ ከማስተላለፍ፤ ጠፍተንም 'ነበሩ' ከመባል በነፃነት ዛሬውኑ ማለፍ ይሻለናል።

biyadegelgne@hotmail.com